# “ተሰማ” ከኢትዮጵያ

ይህ ታሪክ ከኢትዮጵያ የመጣው የ“ተሰማ” ታሪክ ነው። የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ያቀደው ሳይሳካለት በኖርዌይ አገር ለአምስት ዓመታት ከኖረ በኋላ በ 2012 ወደ አገሩ ወደ ኦሮሚያ ክልል ተመልሷል።

ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ከዋና ከተማው በስተ ደቡብ-በስተ ምሥራቅ በትንሽ ርቀት ላይ በምትገኘዋ የደብረዘይት የገጠር ከተማ አንድ የገበሬ ቁዬ ገዛ። “ተሰማ” ቀደም ሲል ስለግብርና ሥራም ሆነ ስለ ዶሮ እርባታ ምንም ዓይነት ልምድ አልነበረውም። ግን የደብረዘይት የአየር ጠባይ ለዚህ ተስማሚ እንደሆነ ያውቅ ነበር።

የመልስ ጉዞ ፕሮግራምን በተመለከተ የስደተኞች እና የከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር (Administration for Refugee and Returnee Affairs  - ARRA) የተሰኘው የኢትዮጵያ  መንግሥታዊ ቢሮ ከኖርዌይ መንግሥት ጋር በመተባበር ይሰራል። “ተሰማ” በአነስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪ ሥራ ስልጠና እንዲያገኝ መስሪያ ቤቱ ያገዘው ሲሆን የድጋፍ ደብዳቤና ፈቃድ ሰጥቶታል። ቢሮው ከዚህም ሌላ በጨርቃ ጨርቅ ምርት፣ በግንባታ፣ በአገልግሎት መስጫ፣ በንግድ ሥራ እና በከተማ  መሬት አጠቃቀም ስልጠና ይሰጣል።

“ተሰማ” ሥራውን ዶሮ  በማርባት ቢጀምርም በአሁኑ ግዜ ለሱቆች እና ለገበያ ማዕከሎች (ሱፐር ማርኬቶች) የሚሸጣቸውን እንቁላሎች ማምረት ጀምሯል። በቀን ከ 6 እስከ 800 እንቁላሎች የሚጥሉ 800 ሴት ዶሮዎች አሉት። ይህ በቀን ከ 700 እስከ 1000 ክሮነር የሚደርስ ብሩቶ ወይም ያልተጣራ ገቢ ያስገኛል። እናም “ተሰማ” በሥራው የሚያግዘው አንድ ሠራተኛ ለመቅጠር ችሏል።



